# በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪዎች ማቋረጥ መንስዔና መፍትሄ

ወርቅነህ ገ/ሥላሴ*

## መግቢያ

በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በየዓመቱ ትምህርታቸውን ለመማር ከሚመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ የዓመቱን ትምህርት ሳያጠናቅቁ በየጊዜው እየተንጠባጠቡ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥራቸው የማይናቅ ነው።

ለምሳሌ ያህል በ1988 ዓ.ም የዓመቱን ትምህርት ለመማር ከተመዘገቡት 2970 ተማሪዎች (ከ7ኛ-12ኛ ክፍል ያጠቃልላል) ውስጥ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ 516 ተማሪዎች (17.3%) አቋርጠዋል። በ1989 እንዲሁ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ውስጥ ለመማር ከተመዘገቡት 1249 ተማሪዎች መካከል 133 ተማሪዎች (10.6%) ያህል አቋርጠዋል፡

እላይ የተጠቀሰው ትምህርት የማቋረጥ መጠን በብዙ መንገድ የማይናቅ ኪሳራ የሚያስከትል በመሆኑ ለትምህርት ማቋረጥ መሠረታዊ ምክንያት የሆነውን ትምህርት ቤቱ ከሚመለከታቸው የመስተዳደር አካላት እና ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበር ትምህርት የማቋረጡ ሁኔታ የሚቀንስበትን ጥረት ለማድረግ እንዲያግዝ ይህ ጥናት ተካሂዷል።

## ጥናቱ ዓላማ

1. በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ከጀመሩ በኋላ በመሃል የሚያቋርጡ ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል መሆኑን ማየትና የሚያቋርጡባቸውን ምክንያቶች ማወቅ፥

2. ተማሪዎቹ የሚያቋርጡባቸው ዋና ዋና ምክንያቶችን በመገንዘብ አቅም በፈቀደ መጠን ትምህርት ቤቱ ከአካባቢው ሕብረተሰብና ከአካባቢው አስተዳደር አካል ጋር በመተባበር እነዚህ ችግሮች የሚቀረፉባቸውን ሁኔታ በመፍጠሩ ላይ እንቅስቃሴ ማድረግ።

*የአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ር/መምህር

# በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪዎች ማቋረጥ መንስዔና መፍትሄ

ወርቅነህ ገ/ሥላሴ*

## መግቢያ

በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በየዓመቱ ትምህርታቸውን ለመማር ከሚመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ የዓመቱን ትምህርት ሳያጠናቅቁ በየጊዜው እየተንጠባጠቡ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ተማሪዎችቁጥራቸው የማይናቅ ነው።

ለምሳሌ ያህል በ1988 ዓ.ም የዓመቱን ትምህርት ለመማር ከተመዘገቡት 2970 ተማሪዎች (ከ7ኛ-12ኛ ክፍል ያጠቃልላል) ውስጥ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ 516 ተማሪዎች (17.3%) አቋርጠዋል። በ1989 እንዲሁ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ውስጥ ለመማር ከተመዘገቡት 1249 ተማሪዎች መካከል 133 ተማሪዎች (10.6%) ያህል አቋርጠዋል፡

እላይ የተጠቀሰው ትምህርት የማቋረጥ መጠን በብዙ መንገድ የማይናቅ ኪሳራ የሚያስከትል በመሆኑ ለትምህርት ማቋረጥ መሠረታዊምክንያት የሆነውን ትምህርት ቤቱ ከሚመለከታቸው የመስተዳድርአካላት እና ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበር ትምህርት የማቋረጡሁኔታ የሚቀንስበትን ጥረት ለማድረግ እንዲያግዝ ይህ ጥናት ተካሂዷል።

## የጥናቱ ዓላማ

1. በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ከጀመሩ በኋላ በመሃል የሚያቋርጡ ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል መሆኑን ማየትና የሚያቋርጡባቸውን ምክንያቶች ማወቅ፥

2. ተማሪዎቹ የሚያቋርጡባቸው ዋና ዋና ምክንያቶችን በመገንዘብ አቅም በፈቀደ መጠን ትምህርት ቤቱ ከአካባቢው ሕብረተሰብና ከአካባቢው አስተዳደር አካል ጋር በመተባበር እነዚህ ችግሮች የሚቀረፉባቸውን ሁኔታ በመፍጠሩ ላይ እንቅስቃሴ ማድረግ።

* የአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ር/መምህር

## የጥናቱ አስፈላጊነት

ትምህርታቸውን ለመማር በአክሱም አ፡ ቀላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከ ሚመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ የዓመቱን ፡ ምህርት ሳያጠናቅቁ በመሃ ል እየተንጠባጠቡ የሚያቋርጡ ተማሪዎች በርካታ ለመሆናቸው አሃዛ ዊ መረጃ አለ። ይህ ጥናት አስፈላጊ የሚሆነው፤

ሀ. በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንድ ምክንያት ይሁን በሌላ ትምህርት አቋርጠው እንደገና ወደ ትምህርት የተመለሱትን በመጠየቅ ለሌላ ጥናት መነሻ የሚሆን ሥራ ለማቅረብ።

ለ. የችግሩን ትክክለኛ ምክንያት ለይቶ በማወቅ ከአካባቢው አስተዳደር አካላትና የሚመለከተው የሕብረተሰብ ክፍል ጋር በመተባበር እነዚህ ችግሮች የሚቃለሉባቸውን ሁኔታ በመፍጠሩ ላይ እንቅስቃሴ ለማድረግ።

## ጥናቱ የተካሄደበት መንገድ (ስልት)

ይህ ጥናት ከ1984 እስከ 1989 ትምህርት ዘመን ባለው ጊዜ ትምህርታቸውን ለመማር ከተመዘገቡ በኋላ በመሃል አቋርጠው በ1990 ዓ.ም እንደገና በትምህርት ቤታችን ለመማር የተመዘገቡ 64 ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ነው። እነዚህ ተማሪዎች ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ውስጥ ተመዝግበው ትምህርታቸው በመከታተል ላይ ያሉ ሆነው ጥናቱ የተካሄደውም ለነዚህ ተማሪዎች መጠይቅበማደል ነው።

ጥናቱን የሚሞሉት ተማሪዎች ነፃና ግልፅ ሆነው ሃሳባቸውን እንዲሰጡ በማሰብ ስማቸውን እንዳይጽፉ ተገልፆላቸዋል። በመጠይቁ ላይ 5 አጠቃላይ የተማሪውን ሁኔታ የሚፈትሹና 15 ለጥናቱ መሠረት የሆኑ ነጥቦችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል። ይህንንም መሠረት ያደረገ አጠር ያለ ትንተና ቀርቧል።

## የመጠይቁ ዝርዝር ትንተና

ከ1984 እስከ 1989 ባለው ትምህርት ዘመን አቋርጠው ቆይተው በ1990 እንደገና ለመማር ቤት/ቤቱ ለተመዘገቡ 64 ተማሪዎች መጠይቅ የታደለሲሆን ከነዚህ ውስጥ 42 (68%) መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል። መጠይቁ ሲታደላቸው የጥናቱ አስፈላጊነት በሚገባ የተገለጠላቸውና በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው ሞልተው እንዲመልሱ የተደረገ ነው።

ሠንጠረዥ 1፡ የአክሱም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከ1984-1989 ተማሪዎች ብዛት በክፍል ደረጃና በፆታ

| ተ.ቁ | ያቋረጡበት ክፍል ደረጃ | ወንድ | ሴት | ድምር | ያቋረጡ በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 9ኛ | 14 | 5 | 19 | 45.2% |
| 2 | 10ኛ | 9 | 2 | 11 | 26.1% |
| 3 | 11ኛ | 5 | - | 5 | 11.9% |
| 4 | 12ኛ | 5 | 1 | 6 | 14.3% |
| 5 | ክፍል ያልጠቀሱ | 1 | - | 1 | 2.5% |
| | ጠቅላላ | 34 | 8 | 42 | 100% |

ከዚህ ሠንጠረዥ መገንዘብ የምንችለው ከ42 ተማሪዎች መካከል 80.9% ወንዶች 19.1% ሴቶች አቋርጠው መቆየታቸውን ነው። በት/ቤቱ የሚገኙተማሪዎች አጠቃላይ የፆታ ጥምርታ ሲነፃፀር 2፡1 የመሆን ሁኔታ ይታይበታል። ይሁንና እነህ አቋርጠው የቆዩ ተማሪዎች ሲነፃፀሩ ደግሞ 4፡1 ሆነዋል። ስለዚህ በማቋረጡ ሁኔታ ከሴቶች ይልቅ ወንዶች አራት እጅ ይልቃሉ ማለት ነው።

የተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥ በየክፍል ደረጃው ጠቅላላ ካቋረጡት ጋር ሲነፃፀር 9ኛ ክፍል 45.2%፥ 10ኛ ክፍል 26.1%፥ 11ኛ ክፍል 11.9% እና 12ኛ ክፍል 14.3% ነው።

ይህም ማለት አዲስ ገቢ.9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአብዛኛው እንደሚያቋርጡ ችግራቸውንም ለመቋቋም እንደሚያቅታቸው ይገመታል።

ሠንጠረዥ 2፡ የአክሱም 2ኛ ደረጃ የተማሪዎች የማቋረጥ መጠን በፆታና በየዓመቱ (1984-1989)

| ተ.ቁ | ያቋረጡበት ዘመን | ወንድ | ሴት | ድምር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1984 | - | - | - | - |
| 2 | 1985 | - | - | - | - |
| 3 | 1986 | 1 | - | 1 | 2.3% |
| 4 | 1987 | 2 | - | 2 | 4.7% |
| 5 | 1988 | 10 | 1 | 11 | 26.4% |
| 6 | 1989 | 22 | 6 | 28 | 66.6% |
| | ጠቅላላ | 35 | 7 | 42 | 100% |

ሠንጠረዥ 2 ላይ መገንዘብ የምንችለው በ1984 ና በ1985 ዓ.ም ካቋረጡትውስጥ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ የሉበትም፥ ነገር

ግን አቋርጠውከቆዩት 2.3% 4.7% 26.4%እና 66.6% በተከታታይ በ1986፥ በ1987፥ በ1988 እና 1989 ትምህርት ዘመን ውስጥ እንደ ሆነ ተመልክቷል።

ይህ የሚያሳየን ካቋረጡት መካከል በ1990 ዓ.ም ወደ ትምህርት ተመልሰው ያሉ ተማሪዎች በ1989 ዓ.ም ተመዝጋቢዎች ናቸው። ይህም ማለት የሚበዛው ከትምህርት ያቋረጠ ተማሪ በቶሎ ወደ ትምህርቱ የመመለስ ፍላጎት ከፍተኛ ነው።

ሠንጠረዥ 3፡ አቋርጠው የተመለሱ ተማሪዎች ብዛት በመኖሪያ ወረዳቸው አንፃር

| ተ.ቁ | ቤተሰቦቻቸው የሚገኙበት ወረዳ | ወንድ | ሴት | ድምር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ላይ ማይጨው (ወረዳ/አክሱም ከተማን ጨምሮ) | 21 | 3 | 24 | 57.2% |
| 2 | ታች ማይጨው ወረዳ | 8 | - | 8 | 18.0% |
| 3 | ዓት ናዕዴር ወረዳ | 5 | 4 | 9 | 21.5% |
| 4 | ዛና ወረዳ | 1 | - | 1 | 2.3% |
| | ጠቅላላ | 35 | 7 | 42 | 100% |

በሠንጠረዥ 3 እንደታየው ከላይ ማይጨው ወረዳ ትምህርት ቤቱ የሚገኝበትን የአክሱም ከተማና በከተማው አካባቢ ያሉ የገጠር ቀበሌዎች የሚይዝ ወረዳ ነው። ይህም አቋርጠው ከቆዩት ተማሪዎች 57.20% ይዟል። ሌሎችከታች ማይጨው፥ ዓት ናዕዴርና ዛና ወረዳዎች ራቅ ያሉ ስለሆነ ከነዚህ ወረዳዎች መጥተው በትምህርት ቤቱ የሚማሩት ተማሪዎች በየሳምንቱ ስንቅ ይዘው መጥተውና ቤት ተከራይተው የሚማሩ ናቸው። ስለዚህ ካቋረጡ በኋላ የመመለስ ፍላጎታቸው በቅርብ ወረዳ በኗሪነት ያሉት ያነሰ ነው ማለት ነው።

በሌላ አገላለጽ አቋርጠው ከቆዩት ተማሪዎች መካከል ከላይ ማይጨው ወረዳ (57%) ከሌሎች ራቅ ያሉ ወረዳዎች በማዳመር (43%)ያለውን ልዩነት ስናመዛዝን በሬሾ ሲሰላ 1፡1 የሚቀራረብ ነው። ይሁንና የአክሱም ከተማና ዙሪያው ወረዳ የሌሎቹን 3 እጅ ያህል የተማሪ ቁጥር ስላለው የተመለሱትም ያን ያህል የበዙ ናቸው። ይህም ማለት ራቅ ካሉ ወረዳዎች የሚመጡት ተማሪ ዎችን ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም አሁንም በከፍተኛ ደረጃ እንደ ሚያቋርጡ መገንዘብ ይቻላል።

ሠንጠረዥ 4፡ ትምህርት አቋርጠው የተመለሱ ተማሪዎች ወላጆች የሥራ ዓይነት (መተዳደሪያ)

| ተ.ቁ | የወላጆቻቸው ሥራ | ወንድ | ሴት | ድምር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና | 19 | 4 | 23 | 54.8% |
| 2 | የቀን ሠራተኛነት | 5 | 1 | 6 | 14.2% |
| 3 | የመንግሥት ሠራተኛ | 4 | - | 4 | 9.5% |
| 4 | ንግድ | 1 | - | 1 | 2.5% |
| 5 | የእደጥበብ ባለሙያ | 1 | 1 | 2 | 4.8% |
| 6 | በወላጆቻቸው ሞት የተነሣ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ | 2 | 1 | 3 | 7.1% |
| 7 | ወላጆቻቸው አካለስንኩላን ስለሆኑ ራሳቸውን የሚያስ ተዳድሩ | .1 | 1 | 2 | 4.8% |
| 8 | ያልተጠቀሰ | 1 | | 1 | 2.4% |
| | ጠቅላላ | 34 | 8 | 42 | 100% |

ከሠንጠረዥ 4 መገንዘብ እንደሚቻለው 54.8% የሚሆኑት ተማሪዎች የገበሬ ልጆች፥ 14.2%፥ የሚያህሉት የቀን ሠራተኛ ልጆች፥ 9.5% የሚያህሉትየመንግሥት ሠራተኛ ልጆች፥7.1% የሆኑ ራሳቸው ሰርተው የሚተዳደሩ ሲሆኑ የቀሪዎቹ ወላጆች በንግድ፥ በዕደጥበብ ሙያ የሚተዳደሩና ሥራ የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

ይህ የሚያሳየን የተማሪዎቹ ማቋረጥ ዋና ምንጩ ከወላጆች የኢኮኖሚ አቅም ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። በርካታ ያቋረጡ ተማሪዎች የገበሬና የቀን ሠራተኛ ልጆች መሆናቸው ከሌላው ይልቅ የኢኮኖሚ ይዞታቸው ደካማ ስለሆነ በዚህ ምክንያት እየተገደዱ እንደሆነ ይታመናል።

ሠንጠረዥ 5፡ አቋርጠው ወደ ትምህርት የተመለሱ ተማሪዎች ካቋረጡበት ምክንያት ጋር ሲገናዘብ

| ተ.ቁ | ያቋረጡበት ምክንያት | ወንድ | ሴት | ድምር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በኢኮኖሚ (የኑሮ ችግር) ምክንያት | 16 | 2 | 18 | 43.0% |
| 2 | በትዳር ምክንያት | 1 | - | 1 | 1.5% |
| 3 | ትምህርቱ ስለከበዳቸው | 2 | - | 2 | 3.0% |
| 4 | የቤተክህነት (የቄስ ትምህርት ለመ ማር በመፈለግ) | 1 | - | 1 | 1.5% |
| 5 | በሕመም (ወላጆች ወይም ራሳቸው) | 14 | 6 | 20 | 51% |
| | ጠቅላላ | 20 | 2 | 22 | 100% |

ሠንጠረዥ 5 ብንመለከት ራቅ ካሉ ወረዳዎች የሚመጡት ተማሪዎች ለሳምንት የሚሆን ስንቅ ይዘው መጥተውና የቤት ኪራይ

ተከራይተው መማር ላይ ችግር እንዳለባቸው የገለጸ መሆኑን ነው። የችግሩ ሚዛን የሚደፋው በኢኮኖሚ ችግር ላይ ነው። በህመም የተነሣ 51%ያህል እንዲያቋርጡ የተገደዱናቸው።

ሠንጠረዥ 6፡ ትምህርታቸውን በሚገባ ለመቀጠል እንዲችሉ ሊደረ ግላቸ ስለሚፈልጉት እገዛ የሰጡት አስተያየት

| ተ.ቁ | ተማሪዎቹ ሊደረግላቸው የሚፈልጉት እገዛ | መልስ ሰጪዎች ብዛት | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 1 | የስንቅና የቤት ኪራይ ችግር ለማቃለል መ ንግሥት በአነፃራዊ ሽፍት እየሰራን የምንማ ርበትን ሁኔታ ቢፈጥር | 21 | 50% |
| 2 | ትምህርቱን አቋርጠን እንደመቆየታችን ት ምህርቱን በመጨበጡ በኩል ችግር ስላለብን መምህራን ተጨማሪ እገዛ ቢያደርግልን | 7 | 16.7% |
| 3 | የልብስና የደብተር ችግር ስላለብን እርዳታ ቢደረግልን | 2 | 4.8% |
| 4 | በግል እየሰሩ ለመማር ለት/ቤት ሰዓት አር ፋጅ በር ላይ የመግባት እድል ይሰጥ | 1 | 2.3% |
| 5 | ሃሳብ ያልሰጡ | 11 | 26.2% |
| | ጠቅላላ | 42 | 100% |

ሠንጠረዥ 6 ላይ መገንዘብ የምንችለው 50% አቋርጠው የቆዩ ተማሪዎች አሁንም ትምህርተን በሚገባ በቀጣይነት ለመማር እንዲችሉ ያለውን የስንቅና የቤት ኪራይ ክፍያ ችግር ለመወጣት መንግሥት በአንፃራዊ ሽፍት እየሰሩ ራሳቸውን የሚያግዙበት ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ይፈልጋሉ። 16.7%ቱ ደግሞ አቋርጠው በመቆየታቸው ትምህርቱን በመጨበጡ ላይ ችግር ስላለባቸው መምህራኑ ተጨማሪ እገዛ ሊያደርጉላቸው እንደሚፈልጉ ያሳያል። 4.8% ያህሉ የደብተር፥ የልብስ እርዳታ ቢደረግላቸው ተጠናክረው ለመማር እንደሚያግዛቸው ተመልክቷል። ከሌሎች አነስተኛ ምክንያቶች ውጪ 26.2% ደግሞ ስለሚያስፈልጋቸው እገዛ ያስቀመጡት ነገር የለም።

## ማጠቃለያ

በአክሱም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በየዓመቱ ትምህርታቸውን ለመማር ከሚመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ በየ ጊዜው የዓመቱን ትምህርት ሳያጠናቅቁ በመሃል እየተንጠባጠቡ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡት ተማሪዎች ቁጥራቸው የማይናቅ ነው።

የሁለት ተከታታይ ዓመታት ማለትም 1988 እና 1989 አሃዝ ብንጠቅስ ለመማር ከተመዘገቡ ከ7ኛ - 12ኛ ክፍል 2970 ተማሪዎች ወይም ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ከተመዘገቡት 1249 ተማሪዎች መካከል 17፤ እና 11፤ ለሁለቱ ዓመት በየበኩላቸው የዓመቱን ትምህርት ሳያጠናቅቁ አቋርጠዋል።

እላይ የተጠቀሰው የማቋረጥ ሁኔታ ሲታይ ትልቅ ኪሳራ መሆኑ እሙን በመሆኑ ይህ ጥናት ችግሩን ለመዳሰስ ሞክሯል።

በተለያየ የክፍል ደረጃና ፆታ ስብጥር ላይ ያሉ በጥናቱ የታቀፉት ያቋረጡተማሪዎች ከመጡበት ወረዳ አኳያ ሲታይ 57.2፤ ከላይ ማይጨው ወረዳ (በአክሱም ከተማና በአካባቢው በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች) ሲሆን በድምሩ 41.8% ደግሞ ራቅ ካሉ ወረዳዎች (የሳምንት ስንቅ ይዘውና ቤት ተከራይተው) የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው።

የእነዚህ ተማሪዎች ወላጆች እንደየኑሮ መሠረት መነሻ ሆኖ ሲታይ ደግሞ 54.8% የገበሬ ልጆች ናቸው፤2.3% የአካለ ስንኩላን ልጆች ናቸው፤ 2.4% የነጋዴ ልጆች ናቸው።

ተማሪዎቹ ያቋረጡበት ችግር ሲታይ 43.0% በኢኮኖሚ ችግር፥ 51% በህመም፥ ወይም በሁለቱም ተደራራቢ ችግር፥3% ትምህርት ስለከበደን ተስፋቆርጠን የሚሉ ናቸው። ወላጅ ስለታመመብን፥ የቄስ ትምህርት ለመማር ስለፈለግኩ የሚሉ ደግሞ ጥቂት ተማሪዎች ለየችግሩ ዓይነት ሃሳብ የሰጡ ይገኙበታል።

## *መደምደምያ*

በአብዛኛው የሚያቋርጡ ተማሪያዎች ራቅ ካሉ ወረዳዎች የሳምንት ስንቅ ይዘውና ቤት ተከራይተው የሚማሩ ናቸው። እነዚህ ተማሪ ዎች ወላጆቻቸውባብዛኛው ገበሬ ስለሆኑ ስለዚህም በቂ ስንቅ ሰጥ ተው ለቤት ኪራይ ከፍለው ስለማይችሉ ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው በመሃል እያቋረጡ እንደሆኑ እንገነዘባለን።

ስለዚህም መሠረታዊ ችግር ለሆኑት የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ መፍትሄ መጠቆም ተገቢ ይሆናል። ስለሆነም *በአጭር ጊዜ*

- የአካባቢው አስተዳደር አካል በሰርቶ-መመገብ ፕሮግራም ለችግረኛ ተማሪዎች በአንፃራዊ ሽፍት በዚሁ ፕሮግራም ታቅፈው የሚታገዙበት ሁኔታ መፍጠር፥

- የከተማው ማዘጋጃ ቤት ከግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር በመወያየት ገና ግልጋሎት መስጠት ያልጀመሩ አዲስ ቤቶች ለጊዜው በመጠግያነት (መጠለያነት) ተማሪዎቹ እንዲሰፍሩባቸው ትብብር በመጠየቅ ችግሩን ማቃለል፣ ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ቤቱ በየቀበሌው ስብሰባ ተገኝቶ እኒህ ተማሪዎች ትርፍ ቤት ያለው ሰው እንዲያስጠጋቸውና እንደ ልጁ በመቁጠር የሚሠራ ስራ እያገዙ እንዲያስተምራቸው (እንዲያግዟቸው) ማስተባበር÷

- መንግሥት ያቋረጠው የትምህርት ቤቶች ክሊኒክ ግልጋሎት እንደገናበጤና ባለሙያ እየታገዘ ቢጀመርና ችግረኛ ተማሪዎች ነፃ ህክምና እንዲያገኙ ቢደረግ÷

የረጅም ጊዜ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መንግሥት በየወረዳ ዎች ሁሉ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በመገንባት ፍትሀዊ ስርጭቱን ለማስፋፋት በየደረጃው ለመተግበር የጀመረውን ሂደት ቢያቀላጥፍ የሚል ነው።